ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፦** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

# ዜና ዘገባ

**መጋቢት 22 ቀን 2004 ዓ.ም**

**የመምህራኑ ጥያቄ ለወያኔ ፈታኝ እየሆነ መጣ**

**የወያኔው ከፍተኛ ባለስልጣን በህዝቡ ተዋርዶ ተመለሰ፤**

**በሙስና ታሰሩ የተባሉት የሰበታ ከተማ ባለስልጣናት አሁንም እየዘረፉ መሆኑ ተጋለጠ፤**

**ወያኔ ምን ገጥሞት ይሆን?**

መምህራን የጀመሩትን ተቃውሞና የስራ ማቆም አድማ አስፋፍተው በመቀጠላቸው የተደናገጠው ወያኔ ሰሞኑን የማስተባበያ ቅስቀሳ ሲያደርግ መሰንበቱ ተሰማ፡፡

በአዲስ አበባ እና በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ከመዋዕለ ህጻናት እስከ መሰናዶ ድረስ ያሉ መምህራኖች ወያኔ ደመወዝ ጨመርኩ ብሎ ሲያናፍስ የነበረውን ባዶ ፕሮፓጋንዳ በመቃወም የትምህርት ማቆም አድማ በማድረጋቸውና በቀጣይም ወደ አደባባይ እንወጣለን በማለታቸው ተደናግጦ ሰሞኑን ደመወዝ ጭማሪ ሳይሆን ደረጃ ማስተካከያ ነው እያለ ማስተባበያ ሲሰጥ መሰንበቱ ተደምጦዋል፡፡

መምህራኖቹ ከየትኛውም መንግስታዊ ተቋዋም እጅግ ያነሰ ደመወዝ ተከፋይ መሆናቸውን በመግለጽ ለብዙ ዓመታት የደመወዝ ጭማሪ እንዲደረግላቸው ጥያቄ ሲያቀርቡ የነበረ ሲሆን ይህንኑ ጥያቄ ተከትሎ ጭማሪ አደረግኩኝ በማለት የ61 ብር እና የ73 ብር ልዩነት ቢያሳይም በድርጊቱ የተበሳጩት መምህራኖች ስራ በማቆማቸው ተደናግጦ የተፋውን ምራቅ ሳይወድ በግዱ መልሶ እየላሰው መሆኑ መምህራኑ አንድነት በመፍጠራቸው ነው ሲሉ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች እየገለጹ ይገኛሉ፡፡

በአሁኑ ወቅት ወያኔ በህዝቡ ላይ የሚጭነውን የድህነት ቀንበር ለማንሳት እና ለመሰባበር መተባበር እንዳለብን ከመምህራኑ አንድነት መማር ያስፈልገል ያሉት የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ቀድሞም ቢሆን የለውጥ ሀዋርያ የሚሆኑት መምህራንና ተማሪዎች በመሆናቸው አሁን የተጀመረው ትግል እንቅስቃሴው ሳይዳፈን ማፋፋም ግድ ይለናል እያሉም በሙሉ ልብ ሲናገሩ እየተደመጡ ናቸው፡፡

በተለይ በየትምህርት ቤቱ ውስጥ ያሉ የአንደኛ ደረጃ ፤የሁለተኛና መሰናዶ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመምህራኑ ጥያቄ በአግባቡ ይመለስላቸው በማለት ጥያቄ ማንሳት በመጀመራቸው ከፍተኛ መደናገጥን የፈጠረባቸው የወያኔ ባለስልጣናት ሳይወዱ በግድ የማስመሰያ ማስተባበያ ቅስቀሳ ለማድረግ መገደዳቸው ታውቆዋል።

በመምህራን ስም መነገዱ ይቁም...... እውነተኛ ጭማሪ ተደርጎ ይፋ ካልተገለጸ በስተቀር በአድማው እንቀጥላለን.....መምህራን በጭማሪው ጮቤ ረገጡ እየተባለ ሲለፈፍ የነበረው ባዶ ፕሮፓጋንዳና ውሸት መሆኑ ለህዝብ ይፋ ሊደረግ ይገባል... የሚሉና ሌሎች አቁዋሞቻቸውን በገለጹ በአንድ ሳምንት ግዜ ውስጥ የደመወዝ ጭማሪ ሳይሆን ማስተካከያ ነው እያለ ወያኔ መለፈፉ ትዝብት ላይ የጣለው ከመሆኑም በላይ የመምህራኑ ጠንካራ አቁዋምን የሚያሳይ ነው ተብሎዋል።

መምህራኖች ባደረጉት የስራ ማቆም አድማ ምክንያት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ያሉ ትምህርት ቤቶች ከ80 በመቶ በላይ ተዘግተው ተማሪዎች እቤታቸው ለመዋል ተገድደው የሚገኙ ሲሆን ወላጆቻቸውም የመምህራኑን ጥያቄ በደመገፍ ወያኔን እያወገዙ መሆኑ ታውቆዋል።

የተደረገው የደመወዝ ጭማሪ መምህራኑን አስደስቶዋል በማለት ሁለት የወያኔ የትምህርት እና የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትር ደኤታዎች መግለጫ የሠጡት በተሳሳተ መንገድ ነው እያለ ወያኔ መልሶ ጥፋቱን በግለሰቦቹ ላይ ለጥፎ የማስመሰያ ይቅርታ ቢጠይቅም መምህራኑ ግን መግለጫውን የሠጡት ባለስልጣናት ቀርበው በይፋ ህዝብንና መምህራኑን ይቅርታ መጠየቅ ይገባቸዋል ይህንን ካላደረጉ ግን በቀጣይም ያዘጋጀነውን የተለያዩ የተቃውሞ እቅዶች ተግባራዊ እናደርጋለን እያሉ መሆኑም ታውቆዋል።
የመምህራኑ አቁዋም ያስደነገጠው ወያኔ በየትምህርት ቤቱ መምህራኑን ለሁለት በመክፈል ደበዳቤ እየጻፈ በመበተን ላይ ሲሆን በተለይ የኮከበ ጽባህ ሁለተኛ ደረጃ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር የሆነው የወያኔ ካድሬ ግንባር ቀደም በመሆን ከ168 መምህራን መሀከል ለ105ቱ «በተፈጠረው ህገ ወጥ ተግባር በአገርና በህዝብ እንዲሁም በተቁዋም ላይ ለሚደርሰው ሰብአዊ እና ቁሳዊ ሀብት ውድመት በህግ ተጠያቂ እንደምትሆኑ እያሳሰብኩ ከዚህ ድርጊታችሁ ተቆጥባችሁ ባስቸኩዋይ ወደ ትምህርት ገበታችሁ እንድትገቡ» የሚል ማስፈራሪያ ደብዳቤ መጻፉ ታውቆዋል።

ምንም እንኩዋን የወያኔው ካድሬ ርዕሰ መምህር ይህንን ማስፈራሪያ ደብዳቤ ለ105 መምህራኑ ይበትን እንጂ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ያሉ 168 መምህራን በሙሉ ስራ አቁመው ትምህርት ቤቱ ተዘግቶዋል።

በአሁኑ ሰዓት በየትምህርት ቤቱ መምህራን በመጥፋታቸው ትምህርት ያልተጀመረ ሲሆን ወያኔም መምህራኑን ለማግባባት ውስጥ ውስጡን እየሰራ መሆኑ ታውቆዋል።

በተመሳሳይ በተለያዩ ግዜ በመምህራኑ ጥያቄ ግራ ሲጋባ የነበረው ወያኔ የሙያ ሰርተፍኬት የሌለው መምህር በሀገሪቱ ውስጥ አያስተምርም የሚል ህግ በቅርቡ ሊያወጣ መሆኑ ታወቀ።

መምህራኑን ለመቆጣጠር እና ረግጦ ለመግዛት እንዲቻለው በየዓመቱ የሚታደስ የሙያ ሰርተፍኬት የሚል አዲስ መስፈርት አውጥቶ ይፋ ሊያደርግ መሆኑ ታውቆዋል።በወያኔ የሚሰጠውን ተከታታይ የሙያ ምዘና ስልጠና የተባለ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ድርሰት ወስዶ የሙያ

ሰርተፍኬት ያልያዘ መምህር በመላ ሀገሪቱ ማስተማር እንዳይችል የሚከለክል አዋጅ ሊያወጣ መሆኑም ታውቆዋል::

ሰሞኑን በመላ ሀገሪቱ በተነሳ የመምህራን ተቃውሞ የተደናገጠው የወያኔ ቡድን የመምህራኑን አንድነት ሊከፋፍል እና ለበታትን የሚያስችለውን አዲስ የሙያ ምዘና ስልጠና የሚል ወያኔ ሰራሽ ማዕቀፍ ለማዘጋጀት በምስጢር ህግ እያረቀቀ መሆኑም ታውቆዋል::

አዲሱ የሙያ ምዘና የሚለው የወያኔ አሳሪ ህግ በህዝቡ ዘንድ ተቃውሞ እንዳያስነሳ ተማሪውን ማዕከል ያደረገ የሚል ሽፋን የሚሰጠው ሲሆን ዋናው መሰረታዊ ጉዳይ ግን መምህሩን የወያኔ ባርያ አድርጎ ለማስቀረት መሆኑን የትምህርት ሚነስትር ውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ ገልጾ ይህንኑ ተግባራዊ ለመድረግ በምስጢር ህግ እየተረቀቀ መሆኑን አጋልጠዋል::

በማስተማር ላይ ያሉትን ጉድለቶች አንጥሮ ለማውጣት እና ለመቅረፍ በሚሉ የማስመሰያ ሀረጎች የታጨቀው አዲሱ እየተረቀቀ ያለው መምህራኑን ቀፍዳጅ ህግ ወያኔ የሚሰጠውን ኮርስ ያልወሰደ በየትኛውም ቦታ በግልም ሆነ በመንግስት ትምህርት ቤቶች እንዳያስተምር የሚያግድ መሆኑ ታውቆዋል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ወያኔ ከሀገሪቱ ህዝብ ይልቅ ለባዕዳን እያጎበደደ.....የኑሮ ውድነቱ እንዲሻሻል ከማድረግ ይልቅ ውጥረቱ ከርሮ ዜጎች እንደቅጠል እንዲረግፉ እያደረገ.......የህዝቡን ችግር ከመቅረፍ ይልቅ በደህንነት ማፈን ላይ አተኩሮ እየሰራ ባለበት በዚህ ወቅት የኑሮ ውድነቱ እጅግ አስደንጋጭ በሆነ መልኩ በመስፋፋቱ ዜጎች በንዴት እራሳቸውን መግደል ጀምረዋል::

ወያኔ በህዝብ እና በሀገር ላይ እየቀለደ ባለበት በዚህ ግዜ ዜጎች በብስጭት እና ተስፋ በመቁረጥ እራሳቸውን እያጠፉ ከመሆናቸውም በላይ ቤተሰቦቻቸው እየተበኑ መሆኑም ታውቆዋል::

ሰሞኑን በሀገሪቱ በከፍተኛ ሁኔታ በተፈጠረው የኑሮ ውድነት ሳቢያ ኑሮውን መቁዋቁዋም ያቃታቸው ሁለት አባወራች እራሳቸውን ገድለው የተገኙ ሲሆን በኪሳቸው ውስጥም«ቤተሰቦቻችንን ማስተዳደር አቅቶናል.....ኑሮ ከአቅማችን በላይ ሆኖብናል.....ልጆቻችን አይናችን እያየ በርሀብ ሲሞቱ ማየት አንችልም.....ከዚህ ሁሉ እራሳችንን ማጥፋቱ አማራጭ የለውም »የሚል ደብዳቤ መገኘቱ ታውቆዋል::

በአዲስ አበባ በቂርቆስ ክፍለ ከተማና በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ነዋሪ የሆኑት ሁለት አባቶች ቤተሰቦቻቸውን የሚያበሉት በማጣታቸው እራሳቸውን በገመድ ሰቅለው የተገኙ ሲሆን ልጆቻቸውም ለአቅመ ስራ ያልበቁ በመሆናቸው እጅግ በከፋ ሁኔታ ውስጥ እንደሆኑና ለግዜው በአካባቢው ህብረተሰብ እርዳታ እየተደረገላቸው መሆኑንም የደረሰን ጥቆማ ገልዋል::

በአሁኑ ሰዓት በአዲስ አበባና ዙሪያዋ አንድ ኩንታል ጤፍ ከ1800 ብር በላይ ተሰቅሎ ....አንድ ኩንታል ስንዴ ከ1300 ብር በላይ ተንጠልጥሎ......ዘይትና ስኩዋር ከገበያ ጠፍቶ......አትክልትና ፍራፍሬ ለእይታ ናፍቆ .....እህልና ጥራጥሬ ምስላቸው ተሰውረውበት .....ባለበት ወቅት በሀገሪቱ ጥጋብ የሰፈነ በማስመሰል ሀሰተኛ ፕሮፓጋንዳ እየነዛ የሚገኘው ወያኔ ለባለስልጣናቱ ከገበሬ ላይ በግዴታ በቅናሽ ዋጋ እየለቀመና እያከማቸ መሆኑም ታውቆዋል::

በህዝቡ ላይ የተጋረጠውን ርሀብና እርዛት እንዲሁም የኑሮ ውድነት ከማርገብና ከመቅረፍ ይልቅ በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ እያወጣ ደህንነቱን እና የአፈና ክፍሉን እያጠናከረ በህዝብ ህይወት ላይ እያላገጠ የሚገኘው የወያኔ ቡድን መልሶ መላልሶ በሀገሪቱ ጥጋብ እንደሰፈነ ማስመሰሉ በእጅጉ የሚያሳፍር እና የሚያሳዝን መሆኑን ህዝቡ እያለቀሰ ይገልፃል::

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ምግብ ፍለጋ የቆሻሻ ገንዳ ላይ ሰፍረው የሚገኙ ዜጎች ቁጥር ከቀን ወደ ቀን ጨምሮ ባለበት...... በየገጠሩ የሚቀምሱት አጥተው እንዳልባሌ በተቀመጡበት የሚቀሩ ዜጎች በዝተው......ህዝቡ እንደቅጠል እየረገፈ ባለበት በዚህ ወቅት የህወሀት ተለጣፊ የሆነው ኦህዴድ 22ኛ የምስረታ በዓል ለማክበር በሚል ድል ያለ ድግስ ደግሶ ባለስልጣናቱን ሲያንበሸብሽ መክረሙም ታውቆዋል::

ከአዲስ አበባ እስከ አዳባ......ከጅማ እስከ አዳማ .....ከባሌ እስከ ጉለሌ.....ከነቀምት እስከ ሐረር......ከሻሸመኔ እስከ ሸዋ .....ድረስ የወያኔ የህወሀት ተለጣፊና ተላላኪ ባለስልጣናት የሆኑት የኦህዴድ ሰዎች እና የወያኔ አባሎች በየአዳራሹ ተሰባስበው በድግስ እየተንበሻበሹ ባለበት ወቅት በሺህዎች የሚቆጠሩ ዜጎች በየጉድባው እየወደቁ ይገኛሉ::

ከትልልቆቹ የወያኔ ባለስልጣናት በተጨማሪ ትንሹ ግልገል ካድሬ ሳይቀር እያንዳንዱ በሚሊዮን የሚቆጠር ጥሬ ገንዘብ በባንክ ከማስቀመጡም በተጨማሪ ብዙ ሚሊዮን ብር የሚያወጣ መኪናና ቪላ ቤት ያልያዘ እንደማይገኝ ህዝቡ በብስጭት ገልጾ ይሄንን ሁሉ ሀብት ከህዝብ አፍ ላይ እየነጠቁ መዝረፋቸው ሳያንሳቸው መልሰው በህዝቡ ላይ ማላገጣቸው ደግሞ ይበልጥ አንጀት የሚያሳርር እና የሚያቃጥል ነው እያለ ህዝቡ በንዴት ቁጣውን እየገለጸ ይገኛል::

ዛሬ 22ኛ የምስረታ በዓላችንን እያከበርን ነው እያሉ ከብስል እስከ ጥሬ.....ከጮማ እስከ ውስኪ......እያገላበጡና እየተጫወቱበት ያሉት የህወሀት ተለጣፊ የሆኑት ኢህዴዶች በዚህች ደቂቃ በሺህዎች የሚቆጠሩ ንፁሀን የሀገሪቱ ዜጎች የሚላስ የሚቀመስ አጥተው ገሚሱ ሲያሸልብ ገሚሱ በስቃይ ኑሮ ውስጥ እየዳከረ ባለበት ወቅት ጮቤ እየረገጡ አስረሽ ምችው ማለታቸው በእጅጉ የሚያሳዝን ከመሆኑም በላይ የሚያሳፍር ነው ሲሉም በቁጭት እየገለፁ ናቸው::

ወያኔ ወደ አዲስ አበባ እየገሰገሰ በነበረበት ወቅት በሰሜን ሸዋ ውስጥ ደራ ከተማ ላይ በ1982 ዓ.ም የተመሰረተው የህወሀት ተለጣፊ የሆነው ኦህዴድ ህዝቡን ለባርነት ያመቻቹ.....በወያኔ ውስጥ ስልጣን የሌላቸው...የተላላኪነት ስራ ብቻ የሚወጡ......ግለሰቦች የተጠራቀሙበት ቢሆንም ባለቻቸው አቅም እየተጠቀሙ ከህዝብ እና ከሀገር ላይ በዘረፉት ሀብት ዛሬ አንቱ የተባሉ ቱጃሮች ለመባል በቅተዋል::

ከአባዱላ ገመዳ እስከ ኩማ ደመቅሳ .....ከግርማ ብሩ እስከ ሶፍያን አህመድ......ከጁኔዲ ሳዶ እስከ ሙክታር ከድር..... ከጄ/ል ባጫ ደበሌ እስከ .....ድረስ የሀገሪቱን ሀብት ግጠው እና ቦጥቡጠው የመለስ ጉዳይ አስፈጻሚ ሆነው ህዝባቸውን ለባርነት የዳረጉ በአዲስ አበባና በሌሎች ዋና ዋና ከተሞች ህንፃዎችና ቪላ ቤቶችን አስገንብተው እያከራዩ የሚገኙ ባለሀብት የወያኔ ሹማምንቶች የህዝቡን መራብና መጠማት ብሎም በችጋርና በችግር መጠበስ ሰምተው እንዳልሰሙ..... አይተው እንዳላዩ ሆነው

በያሉበት ጮቤ እየረገጡ ውስኪ ከጮማ እያገላበጡ መክረማቸው ነገ ታሪክ ይቅር የማይላቸውን ፍርድ ይሰጣቸዋል እያለ ህዝቡ በንዴት እየገለፀ ይገኛል፡፡

ወያኔ የህዝቡን ቁጣ ለማርገብ በሚል ለይምሰል የህዝብ ሀብት ዘርፈው በሙስና ተከስሰው የ15 ዓመት እና የገንዘብ ቅጣት ተጥሎባቸው ወደ ወህኒ ከገቡት የሰበታ ከተማ የኦህዴድ ባለስልጣናት መሀከል አብዛኛዎቹ ከእስር ቤት ወጥተው ቀን ቀን የራሳቸውን ስራ እየሰሩና ሌላም ተጨማሪ ዘረፋ እያካሄዱ የሚውሉ ከመሆኑም በተጨማሪ ህግ የሚባል ለወያኔ ተለጣፊ ባለስልጣናት የማይሰራ መሆኑን ያመላከተ ነው ሲል ህዝቡ በንዴት እየፈገለፀ ይገኛል፡፡

በቅርቡ የኦህዴድ ከፍተኛ ባለስልጣናት በተለያዩ ከተሞች ውስጥ ህዝቡን የማረጋጋት ስራ እንዲሰሩ ለማድረግ ወደ ተለያዩ ከተሞች ተልከው የነበረ ሲሆን ከነዚህ መሀከል አንዱ ጁኔዲ ሳዶ በሰበታ ከተማ ተገኝቶ ህዝቡን ሰብስቦ ባነጋገረበት ወቅት ስለ ሙስና ለማውራት አንተ ብቁ አይደለህም የሚከፈልህን የወር ደመወዝህንና የሰራኸውን መለስተኛ ቤተ መንግስት የመሰለ ቪላ ቤት ማገናዘብ ብቻ በቂ ነው አንተም ሆንክ ሌሎች ያንተ መሳይ ሰዎች በህዝብ ሀብት የተጨማለቃችሁ በመሆኑ ችግር ትፈታላችሁ ብለን ስለማናምን ወቅቱ እስኪደርስ አትድረሱብን ብለው ስብሰባ ረግጠው እንደወጡም ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል፡፡

ወያኔ በውስጣዊ ችግሩ የስንግ ሲያዝ እና የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች የህዝብን ስሜት ይለውጣሉ ብሎ ሲያስብ በየአቅጣጫው የጦርነት ነጋሪት እየጎሰመ የህዝቡን የትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር ላይ ታች ማለት መጀመሩ ታውቆዋል፡፡

ከህዝቡ እውቅና ውጭ በሱማሊያ ውስጥ ገብቶ ዜጎችን እያስጨረሰና የሀገር ሀብት እያወደመ ባለበት ሰዓት መልሶ ፊቱን ወደ ሰሜን በማዞር ከሻእቢያ ጋር ቁርቁዋሶ ለመጀመር መዳከሩ በሀገር ውስጥ ያለውን ትኩሳት ለማርገብና ህዝቡን አንገት ለመስደፋት ሆን ብሎ የተጠቀመበት ስልት መሆኑም እየተነገረ ይገኛል፡፡

ሰሞኑን ከወትሮው በተለየ ሁኔታ በሰሜን እና በምስራቅ ምድብ የሚገኙ የአየር ኃይል አባላት ለውጊያ ዝግጁ እንዲሆኑ ተብለው ከአየር ኃይል አዛዡ የህወሀቱ ጄኔራል ትዕዛዝ መሰጠቱ ታውቆዋል፡፡

ከሜ/ጄ/ል ሞላ ኃይለማርያም የተሰጠው ትዕዛዝ እንደሚያመለክተው ከሆነ በድሬዳዋ ከተማ የሚገኘው የአየር ኃይል ምድብ ወደ ምስራቅ ኢትዮጵያ እያቀና የአየር ቅኝት እንዲያደርግና ለውጊያ ዝግጁ እንዲሆኑ የታዘዘ ሲሆን የሰሜኑም በሀርዳር የሚገኘው የአየር ኃይል ምድብ ዝግጁ እንዲሆኑ እና ማንም የዚህ ክፍል ባልደረባ ፍቃድ እንዳይሰጠው መከልከሉን ከየስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልጾዋል፡፡

እግረኛ ጦርም ባልተለመደ ሁኔታ ወደ ሰሜን ጎንደር እየተመመ መሆኑን የአይን እማኞች ከስፍራው ገለፀው ወያኔ ምን ችግር ገጥሞት ይሆን የሚል ጥያቄም ከህዝቡ የተነሳ ይገኛል፡፡